# የኮቪድ-19 ምርመራ

የኮቪድ-19 ምርመራ ሚኒሶታ ውስጥ በይበልጥ አሁን ይገኛል።

ይህ ቪዲዮ ማን መመርመር እንዳለበት፣ የት መመርመር እንዳለበት  እና ውጤትዎን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ያብራራል።

**ለ ኮቪድ-19 መመርመር ያለበት ማነው ለሚለው ጥያቄ?**

የ ኮቪድ-19 ምልክቶች ያላቸው ሰዎች መመርመር አለባቸው።

ምልክቶቹ ትኩሳት፣ ሳል፣ የትንፋሽ እጥረት፣ የጡንቻ ህመም፣ የራስ ምታት፣ የጉሮሮ መቁሰል፣ ብርድ ማለት ወይም ጣዕም ወይም ሽታ አለመለየት ሊያጠቃልሉ ይችላሉ።

ምርመራ  ማድረግ  እንዳለብዎት  ለማወቅ፣  ከጤና  እንክብካቤ አቅራቢዎ  ጋር  ይነጋገሩ  ወይም  በሚኒሶታ  የኮቪድ ምላሽ (Minnesota COVID Response) ድረ-ጣቢያ  ላይ  በሚገኘዉ የኮቪድ ምልክት ማጣሪያ  መሳሪያ  ይጠቀሙ።

ድህረገፁን  መጠቀም ካልቻሉ  ከቤተሰብ፣  ከጓደኛ  ወይም  ከሌሎች  ሰዎች  እርዳታ  ይጠይቁ።

**የት መመርመር እችላለሁ ለሚለው ጥያቄ?**

ብዙ ክሊኒኮች እና ሆስፒታሎች ለላቦራቶሪ ምርመራ ናሙናዎችን በመሰብሰብ ላይ ይገኛሉ።

የት  እንደሚመረመሩ  ለማወቅ፣  ለጤና  አንክብካቤ አቅራቢዎ  ይደውሉ  ወይም  በሚኒሶታ  የኮቪድ ምላሽ  ድረ-ጣቢያ  ላይ የምርመራ  ቦታዎችንና  ካርታዎች  ይጎብኙ።  ድህረገፁን  መጠቀም ካልቻሉ  ከቤተሰብ  ፣  ከጓደኛ  ወይም  ከሌሎች–ሰዎች እርዳታ  ይጠይቁ።

ወደ  ምርመራ  ቦታ  ከመሄድዎ  በፊት፣  አስቀድመው ይደውሉ  ወይም  ለእዚያ  የምርመራ ቦታ ልዩ የሆኑ መመሪያዎችን ድህረገፁ ላይ ያንብቡ።  ምክንያቱም  ሁሉም ተመሳሳይ  አይደሉም።

**የምርመራ ውጤቶቼን እንዴት ማግኘት እችላለሁ ለሚለው ጥያቄ?**

ምርመራዎን ያከናወነው ክሊኒክ የምርመራ ዉጤቱን ይነግሮታል።

ብዙ ቀናት ሊወስድ ይችላል።

የእርስዎን የላብራቶሪ  ውጤት  ለማግኘት  የሚኒሶታ  የጤና  ክፍልን አይደውሉ።

በመስመር ላይ የኮቪድ ምልክት ማጣሪያ መሣሪያን ወይም የምርመራ ቦታዎችን ካርታ ለመጠቀም፣ mn.gov/covid19 ን ይጎብኙ።

Minnesota Department of Health
Communications Office
PO Box 64975 St. Paul, MN 55164-0975
health.communications@state.mn.us
www.health.state.mn.us

05/26/20

Testing for COVID-19 (Amharic)

*To obtain this information in a different format, call: 651-201-4989*